# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)
# The Ethiopian Federal Democratic Unity Forum

## ከአምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲ ሥርዓት ጤነኛ ኢኮኖሚ ማግኘት አይቻልም!

### ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተሰጠ መግለጫ

በሀገራችን ለተከታታይ አምስት ዓመታት፣ የዋጋ ግሽበት አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ ሲጨምር እንደነበረ ይታወቃል፡፡ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች ከዜጎች አቅም በላይ አሻቅበዋል፡፡ በተጨማሪም የቤት ኪራይ፣ ነዳጅ፣ መሬት ሊዝ ዋጋ፣ የግንባታ እቃዎች፣ የእርሻ ግብአቶች (ለምሳሌ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር) ወዘተ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ በመሆኑም መድረክ አሁን ያለውን የዋጋ ግሽበት ተቀባይነት የሌለውና የኢትዮጵያ ህዝብ ጨርሶ ሊቋቋመው የሚችለው ደረጃ እንዳልሆነ ይረዳል፡፡

የዋጋ ንብረቱን ለመቋቋም በሚል መንግሥት ስንዴ አምጥቶ ከመቸርቸር ጀምሮ በባንኮች ላይ የብድር ጣራ በማበጀት ግሽበቱን ለማርገብ ሞክሯል፡፡ ይሁንና የችግሩ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲባባስ እንጂ መፍትሔ ማግኘት አልቻለም፡፡ ሕዝቡንም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ከቶታል፡፡ የኢህአዴግ የእድገት ሕልምም በማይቀረው የጊዜ ሂደት እየተገፈፈና ግልጽ እየሆነ እንደመጣ በሰሞኑ የታየው አስገራዊ ትርምስ አንድ ማሳያ ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት የዋጋ ግሽበቱ ‹የኢኮኖሚ እድገቱ ያመጣው ስለሆነ እድገቱ ራሱ ይፈታዋል› ብሎ የተመፃደቀ አገዛዝ፣ በሚያስተዛዝብ መልኩ ዓይኑን በጨው አጥቦ ችግሩን ሁሉ በነጋዴው ላይ እያላከከ ይገኛል፡፡

በግብይት ሠንሠለቱ ላይ ያሉ ችግሮች ካሉ መፈታት እንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ መድረክ የሞኖፖሊ ባህሪ ያለውን አሰራርና የሸማቾችን ብዝበዛ አጥብቆ ያወግዛል፡፡ እንደነዚህ የመሰሉ አሠራሮች ካሉ የዋጋ ጣሪያ በመወሰን የሚፈቱ ሳይሆኑ አቅርቦትንና ውድድርን በማስፋት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተደረገ የተባለው ጥናት በኮቾላ የተሰራና ችግሩን ሁሉ በነጋዴው ላይ ያላከከ እና የመንግሥትን ችግር ሳይጠቅስ ያለፈ ነው፡፡ ተጠና የተባለው ጥናት ግልጽነት የሚጎድለውና ለህዝብ ይፋ ያልሆነ ነው፡፡

በሀገራችን መንግሥት በአንድ መልኩ ሕግና ፖሊሲ አውጪ እና አስፈፃሚ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ነጋዴም ነው፡፡ የቴሌፎን፣ የመብራት፣ የውሃ አገልግሎቶችና የነዳጅ ሸመታው በእጁ እንደሆኑ፣ የስኳሩ አምራችና ትልቁ የስኳር ነጋዴ ራሱ እንደሆነና ከእነዚህ ስምሪቶቹ በትርፍ፣ በቫትና በገቢ ግብር መልኩ ብዙ ሃብት እንደሚያግበሰብስ ይታወቃል፡፡ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግም ራሱ በትልልቅ ኢንዶውመንት አማካኝነት ፋብሪካዎችን፣ የፋይናንስ፣ የትራንስፖርት፣ የንግድ፣ የኮንስትራክሽን ወዘተ ኩባንያዎች ያንቀሳቅሳል፡፡

የኢህአዴግ መንግሥት እውነት ለሕዝብ የሚጨነቅ ቢሆን ኖሮ ከሕዝብ ጋራ ችግሮች የመጋራቱን ተግባር ከራሱ ቤት ይጀምረው ነበር፡፡ ለምሳሌ የመንግሥት የስኳር ኤጀንሲ ስኳሩን ከመንግሥት ፋብሪካዎች የሚረከብበት በኪሎ ከአምስት ብር ባነሰ ዋጋ ሆኖ ለነጋዴዎች በጨረታ እየሸጠበት የቆየው ዋጋ ግን በኪሎ አስራ ሶስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም በላይ ነው፡፡ በዚህ ዋጋ የገዙትን ነጋዴዎች ከተረከቡ በኋላ ያወጡትን

ተጨማሪ ወጪ ሳያስሉ አንዱን ኪሎ በአስራ አራት ብር ሸጡ ብሎ አዋጅ ማውጣት እጅግ በጣም አስገራሚ ነው፡፡

ዋናው የዋጋ ግሽበቱ ምንጭ አገዛዙ የሚከተለው የተሳሳተ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫ እንደሆነ መድረክ ያምናል፡፡ ኢህአዴግ የሚከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር በቁጥጥር ፍቅር የተለከፈና የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ ወደ ጎን በመግፋት የሚያምን ነው፡፡ ይህንን ግዙፍና አፋኝ ሥርዓት የሚደግፍ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ወጪዎችን ግድ ይላል፡፡ በ1997 ዓ.ም 11.8 ቢሊየን ብር የነበረው የመንግሥት አስተዳደር ወጪ በ2002 በአራት እጥፍ አድጎ 40 ቢሊየን ብር ደርሶዋል፡፡

የውጭ እርዳታ እንዳለ ሆኖ፣ ይህን ወጪ በዋነኝነት የሚሸፍነው ዜጎች በሚከፍሉት ግብር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ መንግሥት በየወረዳውና ቀበሌዎች ለፖለቲካ ሥልጠናና ለቁሳቁሶች፣ ፕሮፓጋንዳ፣ ለደህንነትና ለካድሬዎቹ የሚረጨው ብር የዜጎች እንደሆነ መገንዘብ ተስኖታል፡፡ ለፖሊስ፣ ለደህንነትና ለፕሮፓጋንዳ የሚወጣው ወጪ አቅምን ያገናዘበ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ዜጎች ለመንግሥት ተቸግረው የሚከፍሉትን እያንዳንዱን ብር ባግባቡና በቁጠባ እንዲያወጣ ይጠበቅበታል፡፡ መራራው ሀቅ ግን ኢህአዴግና ካድሬዎቹ እስከ አንገታቸው በሙስና መስመጣቸው ነው፡፡ አምባገነንነትና ከፍተኛ አስተዳደራዊ ወጪ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ለመሆናቸው ሀገራችን አንዷ ማሳያ ናት፡፡ ይህም ሀገራችን መውጣት ከማትችለው አዘቅት ውስጥ ከቷታል፡፡

በኢኮኖሚው መስክ ገዢው ፓርቲ ምርትና ምርታማነትን ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ባለመቻሉ፣ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት አስከትሏል፡፡ ተገኙ የተባሉት ለውጦች ከሀገራዊ ምርትና ምርታማነት መጨመር የመጣ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሀገሪቷ ውስጥ የተከሰተው የዋጋ ንረት በዋነኝነት ተጠያቂ መሆን ያለበት መንግሥት ቅጥ ያጣ ወጪ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት በእያንዳንዱ እቃና አገልግሎት ላይ በተደጋጋሚ የሚያስከፍለው ታክስ (ቫት) ከፍተኛ የዋጋ ንረት እንዳስከተለ አንድና ሁለት የለውም፡፡

መንግሥት በተከታታይነት በሚወስዳቸው ያልተጠበቁ እርምጃዎች ገበያውን ወደ ትርምስ እየወሰደ ነው፡፡ ይህ እርምጃ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንትም የማያበረታታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ኢህአዴግ እስካሁን በተከተለው የፖሊሲ አቅጣጫ ገቢና የወጪ ንግዳችን ሚዛን በየጊዜው እጅግ እያሰፋው እንጂ ሲያጠበው አልተመለከትንም፡፡ በብር ምንዛሬ ላይ የተደረገውም ለውጥ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት አስከትሎዋል፡፡ በተለይም በነዳጅ ዋጋ ላይ የመጣው ጭማሪ እንዳለ ወደ ተጠቃሚው ማስተላለፍ የዋጋ ንረቱን አባብሶታል፡፡ አጠቃላይ የመንግሥት የበጀት ጉድለት ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ በሆነ ፍጥነት እያደገ ይገኛል፡፡

ኢህአዴግ በጉልበትና በምርኮ ያገኘው ሥልጣኑን፣ ልማት በማምጣት እውቅና/ሌጂቲሜሲ ያስገኝለት ዘንድ እየተፍጨረጨረ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከአስራ ስምንት ዓመት ከማስመሰል የብዙሃን ፓርቲ ጉዞ በኋላ ማስመሰል ወደ ሌለበት የአንድ ፓርቲ አገዛዝ እንደመለሰን ሁሉ፣ ከአስራ ስምንት ዓመት ጉዞ በኋላ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወደ ‹አሻጥረኛ› ‹አወናባጅ› ነጋዴ ወደ ሚለው ጨዋታ እየመለሰን ነው፡፡ የኢሠፓና የኢህአዴግ ልዩነት ‹በአንድ ፓርቲ› እና ‹አውራ ፓርቲ›፣ በ‹ሶሻሊስት መንግሥት› እና ‹ልማታዊ መንግሥት› መሀከል ያሉ ልዩነቶችን ለማየት እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው፡፡ ዜጎች

በሚመለከታቸው ጉዳይ እንኳን አስተያየት መስጠት የሚፈሩበትና አስመሳይነትና አድርባይነት የነገሰበት ወቀት ላይ ደርሰናል፡፡

መድረክ አሁን ካለንበት ጊዜ ይልቅ መጪው ጊዜ እጅግ  አሳሳቢ እንደሆነ ይረዳል፡፡ በተለይ መንግሥት ባወጀው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ቅጥ ባጣ የመንግሥት ወጪና የታክስ ገቢን ተልሞ በመነደፉ እና ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ትክክለኛውን ሚና ስለማይሰጥ ለከፍተኛ የዋጋ ግሽበት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በዓለም አቀማፍ ደረጃ በመከሰት ላይ ያለው የእቃዎች የዋጋ ጭማሪ (ለምሳሌ ነዳጅ) በኢትዮጵያ ላይ ቀላል ያልሆነ ተጽኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

በሀገራችን እየታየ ያለውን የዋጋ ግሸበት የዋጋ ጣሪያ በማስቀመጥ ብቻ መፍትሔ ማምጣት እንደማይቻል መድረክ ያምናል፡፡ ችግሩ መሠታዊና ጥልቀት ያለው ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት ሁሉን አቀፍ መፍትሔ ማበጀት ያስፈልጋል፡፡ በግብይት ሠንሠለቱ ላይ አሉ የሚባሉትን ችግሮች መፍታት አንድ እርምጃ ሆኖ፤ መንግሥት በምግብ ላይ የጫነውን ተዳራራቢ ቫት በማንሳት፣ ቅጥ ያጣውን የመንግሥት የአስተዳደር ወጪ በመነቀነስ፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ እያቀጨጩ አገር መለወጥ እንደማይቻል ሲታመን፤ ለዜጎች ያለውን ተጠያቂነት በማረጋገጥና ሙስና በቀነስ ብቻ የሚፈታ ነው፡፡

መንግሥታት እንደኛ አይነቶቹ ኢክኖሚያዊ ቀውሶች ሲከሰቱ ፖሊሲዎችን ለመመርመር፣ ለመከለስና መንግሥትና የኢኮኖሚውን ዘርፎች መልሶ ለማዋቀር እንደ ልዩ አጋጣሚ ይጠቀማሉ፡፡ የሀገራችን መንግሥታትንም በጉዳዩ ላይ ከሸማቹ ከነጋዴውና ከምሁራን እና እንዲሁም ከሌሎችም አካላት እና ከሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ግልጽና ነፃ ውይይት በማድግ መፍትሔ ማፈላለግ ይኖርበታል፡፡ ይህንን በማድረግም ቀውሶችን ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ለመቋቋም የሚችል ውጤታማ ኢኮኖሚና መንግሥት እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲና መሪዎቹ ግን የፖሊሲ ክለሳ በመቃብራችን ላይ ነው ባይ ናቸው፡፡ የአፈፃፀም ካልሆነ የፖሊሲ ብሎ ስህተት ከእኛ ዘንድ አይታሰብም ባዮች ናቸው፡፡ ከእነሱ የተለየ ሃሳብ ያመጣ ጠላት አድርገው ይመለከቱታል፡፡

መደረክ የንግዱ ማህበረሰብን ጨምሮ የሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች መብቶችና ጥቅሞች የሚያስጠብቅ የፖሊሲ መስተጋብር መኖር አለበት ብሎ ያምናል፡፡ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሸማቹን፣ የባለሃብቱንና የመንግሥትን ጥቅሞች ያገናዘበ፣ ሁሉም ችግሩን የሚጋራበት የመፍትሔ ማእቀፍ መኖር አለበት ብሎ ያምናል፡፡ መንግሥት በእንደዚህ ዓይነት አካሄድ መፍትሔ ማምጣት እንዳለበትም መድረክ ያምናል፡፡

የኢህአዴግ መንግሥት ይዞት የመጣው ጊዜያዊ መፍትሔ ላይ ላዩን የሕዝብ ተቆርቋሪነት ያለ ቢያስመስልም፤ ሸማቹን ጨምሮ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች እና አገሪቱን በአጠቃላይ የሚጎዳ ነው ብሎ መድረክ ያምናል፡፡ ኢህአዴግ ለጊዜውም ቢሆን ቁጣውንና ንዴትን ወደ ሌላ ያዞረው ቢመስለውም የችግሩ ምንጭ ሥርዓቱ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ሕዝቡ በኑሮ ውድነቱ እጅጉን ከተማረረ ቆይቶአል፤ ምሬቱ እየተጠራቀመ ሄደ ወደ ቁጣና ንዴት እየሄደ ነው፡፡ ይህ ቁጣና ንዴት በመንግሥት ላይ እንዳያነጣጥር ለማድረግ ኢህአዴግ ነጋዴውን በመባእነት በማቅረብ የሕዝቡ ትኩረት በዚሁ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ እንዲያነጣጥር አድርጓል፡፡ ይህንን በማድረግ ኢህአዴግ ለጊዜውም ቢሆን ራሱን ከተጠያቂነት ከማውጣቱ ባሻገር የሕዝቡ ተቆርቋሪ ሆኖ እንዲታይና ከሁኔታው አትራፊ ሆኖ ለመውጣት አልሟል፡፡ ይሁን እንጂ ወጣ የተባለውን የዋጋ ጣሪያ የራሱ የሆነ የማስፈፀም ችግር እንዳለበት ቀን በቀን የምንታዘበው ሃቅ ነው፡፡

የኢህአዴግ የሰሞኑ እርምጃ የምርቶች ከገበያ መጥፋት ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሬና አትክልት ይቅርና መንግሥት የሚያመርተው ስኳር ራሱ ከገበያ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ከውጪ የሚመጡ እንደ ዘይትና ሳሙና የመሳሰሉትም ሊጠፉ ይችላሉ፡፡ የንግዱ ማህበረሰብ የሚሰጠውን ለሕብረተሰብ አስፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ጭራሹን አጣ ማለት ደግሞ ነጋዴዎችን ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰብን በጠቅላላ የሚጎዳ ይሆናል፡፡ ኢህአዴግ እንደዚህ አይነት ክፍተት ቢፈጠር እንኳ ጅንአድንና የቀበሌ ሱቆችን በመጠቀም ችግሩን እቋቋማለሁ ሊል ይችላል፡፡ ይህ መንገድ ነጋዴውን ሊተካና ሸማቹን ሊታደግ እንደማይችል ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ዘመን እርምጃዎች አሳምሮ ያውቃል፡፡ ይልቁንም ሸቀጦቹ ከሱቆች ወጥተው በድብቅብቆሽ በከፍተኛ ዋጋ የሚቀርቡበት ሁኔታ ተፈጥሮ ሕዝቡ ለባሰ ዝርፊያና እንግልት እንዲዳረግ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ ጥራታቸው ላልተጠበቀ ምርቶች የደራ ገበያ በመፍጠር የሕዝቡን ጤንነትና ድህነት ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

በንግዱ ማህበረሰብ እየተወሰደ ያለው እርምጃ፣ የሕግ የበላይነትን መርህ የሚፃረር፣ ለግል ባለሃብት ጥበቃ ስፍራ የማይሰጥ አካሄድ የተከተለ በመሆኑ ትልቅ መዘዝ አለው፡፡ ይህ መንግሥት የረጅም ጊዜ እይታ ይዞ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ለማድግ የማይታመን ለውልና ለኮንትራት የማይገዛ መንግሥት ተደርጎ እንዲታይ እንደሚያደርገው መታሰብ ይኖርበታል፡፡ ለገዛ አገሩ ባለሀብት ባላንጣ የሆነ መንግሥት አልሚ መንግሥት ይሆናል ብሎ ለማሰብ ደግሞ ከንቱ ምኞት ነው፡፡ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ እየደረሰ ያለው ጫና ሠራተኛውንም ከሥራ ገበታው የማባረር ውጤት ሊኖረው እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡

መድረክ ጥፋቶችና አጥፊዎች መታረም እንዳለባቸው አጥብቆ ያምናል፡፡ በጥፋትና አጥፊዎች ላይ የሚወስደው እርምጃ ግን መንግሥትና የመንግሥት ባለስልጣናትንም ጭምር የሚያርም፣ ሚዛን የጠበቀና የሕግ የበላይነትን መርህ መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል ብሎ ያምናል፡፡ የመጀመሪያው አጥፊ መንግሥትና ባለስልጣናቱ በሆኑበትና መንግሥት ኃላፊነቱን ባልተወጣበት ሁኔታ ዘሎ ዜጎች ላይ ብትሩን ማሳረፍ ፍትሓዊም ሚዛናዊም አይደለም፡፡

ባጠቃላይ በሀገራችን የተከሰተው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት መፍትሔ የሚገኘው ዜጎች በነፃነት የሚሳተፉበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተፈጥሮ መንግሥትን የመቆጣጠር ሚና ሲኖራቸው፣ የሚያቀርቡትም ሃሳብ ተቀባይነት ሲያገኝ እና ብሄራዊ መግባባት ሲሰፍን ብቻ ነው ብሎ መድረክ ያምናል፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)

ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም